# ከኢትዮጵያዊ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ)

## የተላለፈ የሐዘን መግለጫ

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን ገዜ ወረዳ ኬንቾ ሳቻ ጎዝዲ ቀበሌ በሐምሌ 15/2016 ዓ.ም በደረሰው የመሬት መንሸራተት 2019 ወገኖቻችን ህይወታቸውን ያጡ መሆናቸውን ዜና የሰማነው በከፍተኛ ሃዘን መሆኑን እየገለፅን በደረሰው ተፈጥሮአዊ አደጋ ህይወታቸው ለጠፋው ዜጎችን ቤተሰቦችና ለመላው የጎፋ ዞን ሕዝብ መጽናናትን እንመኛለን። በአደጋው ለህልፈተ ሞት የተዳረጉትንም ቸሩ ዐምላክ ነፍሳቸውን በዐጸድ ገነት ያሳርፍልን። አካላዊ ጉዳት የደረሰባቸውንም ፈጣን መፈወስን እንመኛለን።

ይህ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደረሰው የመሬት መንሸራተት በተደጋጋሚ መሆኑ ችግሩን አሳሳቢ ያደርገዋል። በመሆኑም የኢትዮጵያ አደጋ ስራ አመራር እና ዝግጁነት ኮሚሽን ለወደፊቱ እንደነዚህ ያሉትን አካባቢዎችን በማጥናት ከአደጋው በፊት ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ እንጠይቃለን። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአደጋው ለተጎዱት ዜጎች በሚደረገው የመልሶ ማቋቋም ተግበራዊ እንቅስቃሴ ሁሉ ከበጎ አድራጊዎች ጋር በሙሉ አቅማችን ተባብረን የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እና ሕዝቧን ይጠብቅ !

ሀምሌ 18 ቀን 2016 ዓ.ም አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያዊ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢ.ሕ.አ.ፓ

ስልክ / Phone : +251 944 223 216 ኢሜይል / email: eprp@eprp-ihapa.com